# ወገኔ

አማርጬ የወደድኩትን ሆዴን ስመግበው፧
አፌ እየጣፈጠው ጨጓራዬን ጠቅጥቄ ሳስጨንቀው፧
ሌት ተቀን ጠግቤ ሰውነቴን ሳሰባው፧
የዘመኑ አስተሳሰብም እየሰረገ ህሊናዬን ሲወቅሰው፧
መወፈር ሳይሆን መክሳት ነው እያለ የሚወደደው፧
አይ የኔ ነገር ሰው ምን ይላል እያልኩ ነው የምጨነቀው::

ወጣ ገባ ባልኩኝ ቁጥር ጨርቃጨርቅ እገዛለሁኝ፧
ዛሬ የለበስኩትን ነገ መድገምን እየጠላሁኝ፧
አምሮና ደምቆ መታየትን እወዳለሁኝ::
ኑሮዬ መሟላቱን ሁሉ ሰው እንዲያውቅልኝ፧
ያማረ መኪና ያማረ ቤትና ውድ ዕቃ አካብታለሁኝ፧
አይ የኔ ነገር የሰበስብኩት መስሎኛል ክብር የሚያስገኝ::

ብቻዬን በልቼ ብቻዬን ጠገብኩኝ፧
ብቻዬን ጠጥቼ ብቻዬን ረካሁኝ፧
ብቻዬን ደግሼ ብቻዬን ጨፈርኩኝ፧
አይ የኔ ነገር ለአንድ ስጋዬ ብዙ ተዳከምኩኝ::

ስጋዬ አማረ ደላው ወዛም ሆነ፧
ንብረቴም በዛልኝ ቤቴም አምሮ ታየ፧
ለበስኩ ተሽቀረቀርኩ ሁሉም ሰው ጉድ አለ፧
ቀን ለሞላለት ወቃሽ እንኳን የለ፧
ወገኔ ተጠብሶ በረሀብ ላይ ሳለ፧
ዝም አለኝ ታዛቢው አድራጎቴን እያየ::

ታዘበው ፈጣሪ ይቅር ባይ ነህና ይቅር እንድትለኝ፧
በተግባሬ አጥፍቻለሁና በአምሳልህ ፈጥረኸኝ፧
ወንድሜ ተርቦ ተጠምቶ ተራቁቶም እያየሁ ችላ አልኩኝ::
እኔ ለግል ብቻ ሳስብ የሰጠኸኝን እናት አገሬን እረሳለሁኝ::
አይ የኔ ነገር ለጊዜያዊ ጥቅሜ በብዙ ታለልኩኝ፧
አይ የኔ ነገር ፍርድ ከአንተ እንጂ ከሰው እንዳልሆነ ዘነጋሁኝ፧
አይ የኔ ነገር ማንነቴ በወገኔ እንደሆነ ሳትኩኝ፧

አይ የኔ ነገር ስጋዬን አድልቤ ነፍሴን አቆሰልኩኝ፡፡

ከ ኒኒ ለገሰ

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com